www.ethiopianorthodox.org

# እናትነት ከድንግልና

በሥነ ፍጥረት ሕግ ሁለት የማይስ
ማሙ (ተቃራኒ) ነገሮች በአንድ ጊዜ
በአንድነት አይታዩም ፤ አንዱ ሌላውን
አስለቅቆ ይታያል እንጂ ለምሳሌ ብርሃን
ሳለ ጨለማ ፤ ቅዝቃዜ እያለ ሙቀት
አይኖርም ። እንዲሁም በሰው ልጆች ሕ
ይወት ፤ ሕፃንነትና ሽምግልና ፤ እናትነ
ትና ድንግልና የመሳሰሉት ሁሉ አንዱ
ከሌላው ቀጥሎ የሚመጣ እንጂ ሕፃን
ሲሆን ሽማግሌ የሆነ የለም እናት ስት
ሆን ድንግል የሆነችም የለችም ቅድመ
ዓለም የነበረ የአብ አካላዊ ቃልን ከወለ
ደች ከድንግል ማርያም በቀር ።

የሰው ልጆች ወንዱ ለአቅመ አዳም
ሴትዋ ለአቅመ ሔዋን እስኪደርሱ በድ
ንግልና ይኖራሉ ፤ ለአካለ መጠን ሲደር
ሱ ወንዱ ሚስት ፤ ሴትዋ ባል ሲያ
ገቡ ድንግል መባላቸው ይቀራል ሴቶች
ሁሉ ለአቅመ ሔዋን እስኪደርሱ በድን
ግልና ይኖራሉ ባል ከአገቡና ልጅ
ከወለዱ በኋላ ደናግል መባላቸው ይቀ
ራል ልማደ አንስት ዘርአ ወራዙት ደር
ሶአቸው እናቶች ሆነዋልና ። ስለሆነም
እናትነትና ድንግልና በአንዲት ሴት
ሕይወት ላይ በአንድነት ሊኖሩ የማይች
ሉና የማይስማሙ ሁኔታዎች ናቸው ።
የእናትነት ሥራ ድንግልናን ያስወግ
ዳል ፤ ድንግልናም እናት ለመሆን አያበ
ቃም ።

በድንግልና እናት ለመሆን የበቃች
ከእናትነትም ጋር ድንግልናን አስተባ
ብራ ይዛ የተገኘች ከቅድስት ድንግል
ማርያም በቀር ሌላ ሴት የለችም ። ያለ
ዘርአ ብእሲ በድንግልና ልጅ መውለ
ድና በድንግልና ጸንቶ መኖር "ድንግል
ወእም" መባል ግን ከተፈጥሮ ሕግ
በላይ የሆነ እስደናቂና አምላካዊ ምሥ
ጢር ነው ።

ይህ ምሥጢር ቀደም ሲል በምሳሌ
ተገልጦአል በትንቢትም ተነግሮአል ።
ምሳሌ የአዳም ከጎቱም ምድር ፤ የሔ
ዋንም ከጎቱም አጽመ ገቦ መፈጠር አ



ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ

ካላዊ ቃል በድንግልና ተጸንሶ በድንግ
ልና ለመወለዱ ምሳሌ ነው ። ዘፍ 2 ፥7-
24 ይህን ምሥጢር ዮሐንስ አፈወርቅ
በሚከተለው ሁኔታ አብራርቶ ገልጾ
ታል ። "ቀድሞ አዳምን ካልታረሰች
(ከድንግል) ምድር ፈጠረው ዳግመኛ
ሔዋንን ከአዳም ያለ እናት ፈጠረ ።
አዳም ያለ እናት ሔዋንን እንዳስገኘ
እንዲሁ ዛሬ ድንግል ክርስቶስን ያለ
አባት ወለደች" (ሃይ አበ ክፍ 9 ፥28)
"ከአዳም ጎን የጐድን አጥንት እንደ
ነሣ አዳምንም አካል እንዳልጐደለው
እንዲሁ ከድንግል የምትናገርና የምታ
ውቅ ነፍስ ያለችው ሥጋን ተዋሐደ ማ
ሕተመ ድንግልናዋም አልተለወጠም ።
አዳም የጐድን አጥንት ከእርሱ ከተ
ነሣ በኋላ አካል ሳይጐድለው ፍጹም
ሆኖ ኖረ ። ድንግልም ሕፃን ክርስቶስ
ከእርስዋ ከተወለደ በኋላ እንዲሁ ያለ
መለወጥ በድንግልና ጸንታ ኖረች ።

(ሃይ አበ ም ፡ 66 ክ ፡ 9 ፥3

እግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆኑ
አምላክነቱን አላስቀረበትም ድንግል
ማርያምም እናትነትዋ ድንግልናዋን
አላስቀረባትም ። ስለሆነም እርስዋ
ድንግል ወእም" "ስትባል መኖርዋ
እርሱ "አምላክ ወሰብእ" ሲባል ለመኖ
ሩ ማስረጃ ነው ። ይህንንም ሊቁ በሚከ
ተለው ገልጾታል "በወለደችውም ጊዜ
ድንግልናዋን ያለመለወጥ አጸና ፤ ድን
ቅ በሚሆን ጽንስዋ ለደገኛው ሃይማ
ኖት መሪ ትሆን ዘንድ" (ዮሐንስ አፈ
ወርቅ ሃይማኖተ አበው ም፡66 ክ 9፥32)
"የእናቱን ማኅፀን የፈጠረ ድንግልና
ዋንም ያጸና እርሱ ነው ፤ ዘር በሌለበት
ልደት ተወልዶአልና ።" ቁ 34 "የአም
ላክ ሥራ ስለሆነ መጽነስዋ በጣም ይደ
ንቃል የመውለድዋ ምሥጢር ኃይልም
አይመረመርም ። ማንም ማን ባሕርይ
ውን የማያውቀውን እርሱን ወለደችው
ማኅተመ ድንግልናዋም አልተለወጠ
ም ። (ጎርጎርዮስ ሃይማኖተ አበው ም፡
60 ክ ፡ 1፥ 15) "ከድንግል ብቻ ተወለደ
ድንግልናዋንም ያለመለወጥ አጸና"
ቁጥ. 20 "ከእናቱ በድንግልና ተወለደ
በመወለዱም ድንግልናዋ አልተለወጠ
ም የወሰነችው የድንግል ማኅፀን አልተ
ለወጠም እንደ ቀደመው አጸናት እንጂ፤
(ጎር ሃይማኖተ አበው ም፡ 61 ክ 3 ፥6)
"በድንግልና ሳለች ከእርስዋ ተወለደ
ድንግል ማርያምን እናቴ አላት ከፈጠ
ራት ጀምሮ በምንም በምን ከድንግል
ናዋ አልተለወጠችም" (ቴዎዶጦስ ሃይ
ማኖተ አበው ም፡ 53 ክ ፡ 1 - 22

በትንቢትም አካላዊ ቃል ከድንግል
እንደሚወለድ እርስዋም በድንግልና
ጸንታ እንደምትኖር ኢሳይያስ "እነሆ
ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወ
ልዳለች"በማለት ትንቢት ተናግሮ ነበ
ር ኢሳ. 7 ፡ 14 ። ሕዝቅኤልም በራእዩ

ወደ ገጽ ፳፬ ዞሯል

www.ethiopianorthodox.org

# እናትነት...

ከገጽ ፲ የዞረ

በምሥራቅ በኩል አዲስ ቤት ተቆልፋ
(ተዘግታ) ቀይ ጐልማሳ ቁልፉን ሳይከ
ፍት በዝግ በር ገብቶ በዝግ በር ሲወጣ
አይቷል ። የተቈለፈች አዳራሽ የእመቤ
ታችን ሳይከፍት ገብቶ ሳይከፍት የወ
ጣው የክርስቶስ ቁልፍ የማኅተመ ድን
ግልናዋ ምሳሌ መሆኑን መምህራን ያስ
ረዳሉ ባለ ራእዩ ያየውና የሰማው የሚ
ከተለው ነው ። "ወደ መቅደስም ወደ
ሚመለከተው በስተውጭ ወዳለው ወደ
መቅደሱ በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበር፤
እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖ
ራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባ
በትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔ
ር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል" ሕዝ
44፥1-3።

ይህንና የመሳሰለውን ትምህርት ተቀ
ብለን የቀደሙንም አባቶች እንዳስተ
ማሩን ቅድስት ድንግል ማርያም የአም
ላክ እናት እንደሆነች በእናትነትዋም
ላይ በድንግልና ጸንታ እንደኖረች እና
ምናለን እናሳምናለንም ። አምላክን
በድንግልና የወለደች ቅድስት ማርያም
በንጽሕና በድንግልና ያጌጠች በነፍ
ስና በሥጋ በነቢብና በገቢር በርእ
ስና በሥጋ በነቢብና በገቢር በርእ
ፍአ፤ በነፍስ በሥጋ ድንግል ናት በን
ጽሕና በድንግልና ለመኖር የነበራት
ጽኑዕ ሕሊና የአምላክ እናት ለመሆንና
በድንግልናም ጸንታ እንድትኖር አበ
ቃት ። በዚህም "መትሕተ ፈጣሪ መል
ዕልተ ፍጡራን ከፈጣሪ በታች ከፍጡ
ራን በላይ" ሁና ስለ ሰው ልጆች ደኅን
ነት የምትማልድ የክርስቲያኖች መመ
ኪያና የደኅንነት ምልክት ሆነች ።

እግዚአብሔር ወልድ ከድንግል ማር
ያም ነፍስና ሥጋን ተዋሕዶ ሰው ሆነ
ስለእኔም በደል በመስቀል ተሰቅሎ ስለ
እኔ ሞተ በእርሱ ሞት የእኔ ሕይወት ተገ
ኘ ብሎ የሚያምን ሁሉ ቅድስት ማር
ያም ክርስቶስን ከመጽነሷ በፊት በጸነሰ
ችውም ጊዜ ከጸነሰችውም በኋላ ከ
መውለድዋ በፊት በወለደችውም ጊዜ
ከወለደችውም በኋላ ድንግል እንደሆ
ነች ማመን ይገባዋል ። አምላክ በተወ
ሰነበት ማኅፀን ፍጡር ሊወሰንበት አይ
ገባምና ስለዚህም ነው የእግዚአብሔር
ቃል "ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ
አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስ
ራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበ
ታልና ተዘግቶ ይኖራል" በማለት ከጽ
ንስም በፊት በጽንስም ጊዜ ከጽንስም
በኋላ፤ ከልደት በፊት በልደትም ጊዜ
ከልደትም በኋላ ማኅተመ ድንግልናዋ
እንዳልተለወጠና እንደማይለወጥ ያስ
ረዳው ።

ስለዚህ ድንግል ማርያም ለሴቶች
ጠባይ በማይስማማ ሁኔታ አምላክን
በድንግልና ጸንሳ በድንግልና የወለደች
ከእናትነትም ጋር ድንግልናን አስተባ
ብራ የያዘች አማናዊት ድንግል ናት ።

ራ.ደ. አስረስ